# ኢሕአፓ በኖርዌይ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ አኪያሄደ

የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አካላት በኖርዌይ ኦስሎ ከተማ ተገኝተው ስለ አገራችን ወቅታዊ ሁኔታና ስለ ድርጅቱ እንቅስቃሴ ገለጻ ሰጡ።

ስብሰባዉ የተጀመረው በኖርዌይ አገራዊ ኮሚቴ ተወካይ አቶ ጌትነት ዉብሸት በትግሉ የወደቁትን ሰማዕታት በመዘከር ሲሆን ከዚያም በመቀጠል ስለ ኢሕአፓ ቀጣይ ትግል መግቢያ ንግግር በማድረግ ነበር።

በዚሁ መስከረም 6, 2008 በተኪያሄደው በርካታ ተሳታፊዎች በተገኙበት ስብሰባ ላይ የድርጅቱ መሥራች መሪ አቶ እያሱ አለማየሁና የድርጅቱ ቀደምት ሴት ታጋይና የአለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት አመራር አካል ወ/ሮ ገነት ግርማ ሰፋ ያለ ማብራርያ ሰጥተዋል።

ዓለም አቀፍ የሴቶችን ትግል አጽናኦት በመስጠትና በአገራችን በሴቶች መደራጀት ዙሪያ የተሞከሩትን ሙከራዎች በሱስቱም አምባገነን መንግሥታት የነበረዉን የሴቶች ተሳትፎ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በመጥቀስ ገለጻ የሰጡት የትግሉ መሥራች ወ/ሮ ገነት ለቀጣዩ በውጭ ያለነው ሴቶች በሚገባ ተደራጅተንና ጠንክረን ለትግሉ ሂደት የበኩላችንን ሚና መጫወት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ወ/ሮ ገነት አያይዘውም የዓልም አቀፍ የትገል ማኅበሩ ምንም እንኳን እንደ ማኅበር ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም በአሜሪካ፣ በአውስትራልያና በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች ውጤታማ መሆኑን ገልጸው በተጨማሪም ማህበሩ በድኅረ ገጽ፣ በፓልቶክና በሬድዮ ፕሮግራም የጀመሩ በመሆኑ ለዓለም አቀፍ የሴቶች ትግል ሂደቱ መጠንከር አብይ ሚና ስለሚጫወት ሰቶች እንዲበረታቱና እንዲገለገሉበትም ጠቁመዋል።

የኢሕአፓን የትግል ሂደት ለየት የሚያደርገው የትግል ስልቱን የተማረው ከትግል ነው በመሆኑም ብዙ ዋጋዎችና ምስዋዕትነትን አስከፍሎናል በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ እያሱ አለማየሁ ላኛ በርጅሙ የትግሉ ጉዟችን ያሳለፍናቸው ስህተቶችን ዛሬ የሚደግም አላዋቂ ነው በማለት ገልጸዋል።

አቶ እያሱ አያይዘዉም ያለፍንባቸዉ ሦስት መንግስታት ገዳይና አሣሪ መንግሥታት በመሆናቸዉ የትግል ሂደቱን መራራ እንዳደረገው ገልጸው በአንጻሩ የተቃዋሚ ድርጅቶች የጥንካሬ ማነስና የወያኔን መንግስት በጋራ ጠላትነት በሚገባ አለመረዳት ትግሉን በተፈለገዉ ፍጥነት ዉጤታማ እንዳላደረገው ጠቁመዉ አሁን በአገራችን እየታየ ያለው የጎረቤት አገሮች የተቃውሞ ውጥረት፣ የረሃቡ አስከፊነት፣ የምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆልና የሕዝቡ ሰቆቃ የዚህ ውጤት መሆኑን ገልጸዋል።

በመጨረሻም ያሁኑን አምባገነን መንግሥት በጋራ የህብረት ግንባር በመታገል አገራችንን ከዚህ አስከፊ ሰቆቃ መታደግ የያንዳንዱ ዘጋ ድርሻ መሆኑንም ገልጸዋል።

በዕለቱ ከታዳሚዎች ለሁለቱም የከፍተኛ አመራር አካላት በተለይም የኢሕአፓን ረጅም ዕድሜ የተመክሮ ሂደት የነበሩትን አውንታዊና አሉታዊ ነጥቦች በማንሳት ነጻ የሆነ የጥያቄና አስተያየት ጊዜ የነበረ ሲሆን ከመድረኩም በተናጠል ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ተስጥቷል።

በመሀሉም በጋዜጠኛና ጸሐፊ ያሬድ ተሾመ አንተና እኔ የሚል የድርጅታችንን ታሪካዊ የትግል ጉዞና ጽናትን ገላጭ የሆነ ግጥም ተነቧል።

በዝግጅቱ ማጠናቀቂያ በኖርዌይ የድርጅቱ የሴቶችና የወጣቶች ኮሚቴ ተወካዮች ወ/ሮ አለምፀሐይ ቁምላቸውና ወጣት አበባው ተክለብርሃን የእንኳን ደህና መጣችሁ ስጦታዎችን ለክብር እንግዶቹ አስረክበዋል።